# እስልምናን እንደገና ማደስ

## ጸሎቶች

*በመሐመድ ሕይወት የተገለጡትን ትምህርቶችና የሐሰት መገዛት እክዳለሁ፡፡*

*መሐመድ የአምላክ መልዕክተኛ ነው የሚለውን የውሸት እምነት አልቀበልም፡፡ እክደዋለሁም፡፡*

*ቁርአን የእግዚአብሔር ቃል ነው የሚለውን አነጋገር እክዳለሁ፡፡*

*ማንኛውንም ሸሀዳን ማነብነብ አግባብ ነው ብዬ አልቀበልም፡፡ እክደዋለሁም ፡፡*

*አል ፋቲሃ አይሁዶች ከእግዚአብሔር ቁጣ በታች ናቸው፣ ክርስቲያኖችም ከሀዲዎች ናቸው የሚለውን አስተምህሮ እክዳለሁ፡፡*

*አይሁዶችን መጥላትን እክዳለሁ፡፡ መጽሐፍ ቅዱስን በርዘውታል የሚባለውን አባባል አልቀበልም፡፡*

*እግዚአብሔር ኤሁዳውያንን ጥሏቸዋል የሚለውን አመለካከት እክዳለሁ፡፡*

*ቁርአንን ማነብነብና በሕይወቴ ላይ ስልጣን አለው የሚለውን አባባል እክዳለሁ፡፡*

*መሐመድን እንደ ምሳሌ በመቁጠር የሚደረግ ማንኛውንም የሐሰት አምልኮ እክዳለሁ፡፡*

*መሐመድ እግዚአብሔርን አስመልክቶ ያመጣውን የሐሰት ትምህርቶች እክዳለሁ፡፡ በቁራኑ ላይ የተገለጠውን አላህ እግዚአብሔር ነው የሚለውን አባባል እክዳለሁ፡፡*

*በተወለድኩ ጊዜ ለእስልምናና ለዘር ዘሮቼ የተሰጠሁበትን መሰጠት እክዳለሁ፡፡*

*የመሐመድን ምሳሌዎች ተከተል የሚለውን አስተሳሰብ እክዳለሁ፡፡*

*የኃይል ጥቃትን ፣ሌሎችን ዝቅ አድርጎ ማየትን፣ ጥላቻን፣ በሴቶች ያለአግባብ መጠቀምን፣ ሌብነትን፣ መሐመድ የፈጸማቸውን ሁሉንም ኃጢአቶች እቃወማለሁ፡፡ እክዳለሁ፡፡*

*በክርስቶስ ኢየሱስ የሆኑቱ ከኩነኔ ነፃ መሆናቸውን፤ የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ከማንኛውም አሳፋሪ በደል ነፃ ስላወጣኝ ማንኛውንም አሳፋሪ ነገርን አልቀበልም፡፡ ደግሞም እክደዋለሁ፡፡*

*በሙስሊሞች የሚነገር ማንኛውንም የፍርሃት ንግግር አልቀበልም ደግሞም እክደዋለሁ፡፡ በሙስሊሞች ዛቻ የተነሳ በፍርሃት ውስጥ ለወደቁት እግዚአብሔር ይቅርታ እንዲያደርግላቸው፣ በሁሉም ነገራቸው በእግዚአብሔር መታመንን ምርጫቸው እንዲያደርጉ እጸልይላቸዋለሁ፡፡*

*እግዚአብሔራዊ ባልሆነው ማንኛውም ድርጊቴ ይቅርታ እንዲያደርግልኝ ፣ መሐመድንም የአላህ መልዕክተኛ ነው ብዬ በመከተሌ እግዚአብሔርን ምህረት እጠይቃለሁ፡፡*

*ኢየሱስ ዳግመኛ ወደ ምድር በሚመጣበት ጊዜ በምድር ላይ የሚኖሩ ሁሉም ሕዝቦች የመሐመድን ሸሪአ እንዲቀበሉ ያስገድዳቸዋል የሚለውን የስድብ ንግግር እቃወማለሁ ፡፡ ደግሞም እክዳለሁ፡፡*

*ኢየሱስን ብቻ ለመከተል ምርጫዬ አድርጌአለሁ፡፡*

*ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን፣ ለኃጢአቴ በመስቀል ላይ መሞቱን፣ ለኔ ደህንነት ሲል ከሞት መነሳቱን አምናለሁ፡፡ ስለ ክርስቶስ መስቀል እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ፡፡ የኔን መስቀል ወስዶ እንድከተለው ስላደረገኝ፤*

*ክርስቶስ የሁሉም ጌታ መሆኑን አምናለሁ፡፡ በሰማይና በምድር ላይ ገዢ ነው፡፡ የሕይወቴ ጌታ ነው፡፡ በሕያዋንና በሙታን ላይ ሊፈርድ ዳግመኛ እንደሚመጣ አምናለሁ፡፡ እንድንበት ዘንድ ከሰማይ በታች የተሰጠ ከኢየሱስ ሌላ ስም እንደሌለ አምናለሁ፡፡*

*አባቴ እግዚአብሔር አዲስን ልብ እንዲሰጠኝ ወደ ሕይወቴ እጋብዘዋለሁ፡፡ እርሱም የክርስቶስ ልብ ነው፡፡ በምናገረውና በማደርገው ሁሉ ይመራኝ ዘንድ፤*

*ሁሉንም የሐሰተኛ አምልኮዎች እቃወማለሁ፡፡ ህያው አምላክን ለማምለክ ማንነቴን አሰጣለሁ፡፡ አብ፣ ወልድና መንፈስቅዱስን፡፡*